# ዓቅምህን ማወቅ ብልጥነት ነው።

“ጫማኻ ማዕረ እግርኻ” በትግርኛ የሚል ኣነጋገር ኣለ። ትርጉሙ “ጫማህን በእግርህን ልክ” ማለት ነው። ከእግርህ ካነሰ አልያም ትልቅ ከሆነ ጉዳቱ ምን ያህል እንደሆነ ሁላችን የምንዘነጋው ኣይመስለኝም። የዚህ ኣባባል መልእክቱ ለሚገባው ከባድ ትርጉም ኣለው ብየ ኣምናለሁኝ። ይህንን ኣባባል መሰረት በማድረግ ግለ ሰዎች ድርጅቶች መንግስትታትን ወዘተ.......... መመዘንና ስለእንሱ ተገቢውን እውቀት ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድ የሚባልበት ኣይደለም። ስለሆነም በበኩሌ ስለ ኢትዮጵያውያን ፖለቲካዊ ድርጅቶች ያለኝ ግንዛቤ ልግለፅ።

“ጫማህን በእግርህን ልክ” የሚይለውን አባባል በህወሓት/ኢህኣዴግ ምን ማለት ይቻላል? ብሎ ለመናገር ከሚያስችለኝን ነገር ኣንድ ታሪክ ዛሬም ላጫውታቹህ። ዛሬም ወደ 1982 ዓ/ም/ኢ. ልመልሳቹህ ነኝ።

ለካቲት 20/1982 ደብረታቦር የነበረውን የደርግ ጦር ሙሉ በሙሉ በደመሰስንበት ማግስት ማለት በለካቲት 21/1982 ጥዋት ተነስተን ከኣለምሳጋ ተነስተን ወደ ምዕራብ በመጓዝ ላይ እያለን ሰዓቱ ደርሶ የወያነ ድምፅ ሬድዮ ለማዳመጥ ሬድዮ በምንከፍትበት ስዓት ኣመድ በር ደርሰን ነበር። በጉዞ ላይ የነበረው ክፍለጦራችን (ኣሉላ ክፍለጦር) በደብረታቦር ስለሰራው ስራ ውጤት በዜና ተነግሮን እንዳለቀ “ጉና” የሚለውን ኣዲስ ዘፈን ለመጀመርያ ግዜ በጆራችን ላይ ዓረፈ። በዛን ግዜ በክፍለጦራችን የተፈጠረ ደስታ ኣሁን ሳስታውሰው ያ ደስታ አሁንም ኣይረሳኝም። ከኣንድ ቀን በፊት በነበረው ውግያ እስከዛን ቀን ኣብረውን የነበሩ ለዓላምቻው ማሳካት ሂወታቸውን ሰጥቶ ከጎናችን ተለይቶ ከጉና ተራራ እስከ ኣለምሳጋ እየቀበርናቸው የመጣን ታጋይ ጓዶኞቻችን ምን ያህል እንደነበሩ ታሪክ ይናገረው። ለምን ሂወት እንደሰጡና እኛም ዛሬ ቆመን ብንሔድ እንደ እነሱ ሂወታችን ሰጥተን እንደምንከተላቸው ኣውቀን፡ የእነሱን ከእኛ መለየት ሳያሳዝነን ጉና በሚለውን ኣዲስ ዘፈን ከመጠን በላይ ተደስተን ነበርን ያዳመጥነው። አሁንም ያንን ዘፈን ስሰማ በውስጤን የሚፈጥረው ደስታ በጣም ልዩ ነው።

ያ ስራ ለመስራት ክ/ጦራችን የተሰጠው ሓላፊነት ደብረታቦር ውስጥ በመግባት የ102ኛ ኣየርወለድንና የስፓርታ ኮማንዶን በራጊዶችን በመደምሰስ የ3ኛው ኣብዮታዊ ሰራዊት ዕዝ ኣመራር እንዳልነበረ ማድረግ ነበር። እዛው ምዕራፍ ለመድረስ ከ9፡30 ጠዋት ሬጅመንቶቻችን ስራ ጀመሩ። ውግያው ግን ከተያዘለትና ከተጠበቀው ግዜ ባነሰ በጣም ተለዋወጠ። የደርግ ጦር የጀመርነውን ማጥቃት መቋቋም አቃተው። ከጉና ተራራ እስከ ደብረታቦር እስከ ምሳ ሰዓት ተቆጣጠርነው (ግዜው በጣም ስለረዘመ ትክክለኛው ሰዓቱ አላስታውሰውም)። ደርግ ለመሸሽ ተዘጋጀ። ደብረታቦርን ወደ ምስራቅ በሙተው ወዴ ሓሙሲት ኣዲስ ዘመንንና ወደ ወርታ ባህርዳርን ኣቅጣጫ ወደሚወስደው መንገድ መኪኖዎቹን ታንኮዎቹን ሁሉም ያሉት ተሽከርካሪዎች መጓዝ ጀመሩ። ያ በመሸሽ ላይ ያለው የደርግ ጦር ኣለምሳጋን ከተቆጣጠረ ሙሉ በሙሉ የማምለጥና የመሸሽ ዕድሉን በጣም ሰፊ ስለነበረ፡ ደርግ ለማምለጥ እኛ ደግሞ ደርግን ለመደምሰስና የያዛቸውን ተሽከርካሪዎችን ለመቀማት፡ ኣለምሳጋን ለመያዝ ተቀዳደምን። ሬጅመንት ፅንዓትና ከሬጅመንታችን (ሑመር) ኣንድ የሞርታ የመቶና ኣንድ የቢ10 የመቶ ቀድሞ

ቦታውን ተቆጣጠሩት። ያቦታ ቀድመን እንደያዝነው በሚገባ ያወቀ የድርግ ጦር ያንን ቦታ ለመቀማት ማድረግ ያለበትን ለማድረግ ስራ ጀመረ። ታንኮች ቢኤሞች ሁሉም ዓይነት ሞርታሮች መድፎች ሚጎች በኣንድ ቦታ ላይ ዘነቡበት። ግን እዛ ያለው ማን መሆኑን የዘነጉት ይመስላል። እዛ ያለው ግን በ1980 በሽሬ ከተማ ደርግን ያሳፈረ በታባ ወያናይ ፅንዓት ተራራ ላይ ታሪክ የሰራ ሬጅመንት መሆኑን አላዎቁትም። በዛ ምክንያትም ነው ሬጅመንት ፅናት ተብሎ የተሰየመው።

ደርግ ያደረገውን ሙከራዎች በሙሉ ከዱት። አሁን ንብረቱን ይዞ ለመሔድ አለመፍቀዳችንም ገባው። ታድያ ንብረቱን ይዞ መሔድ ካልቻለ ማቃጠል እንዳለበት ወሰነ። በበኩላችን በኣለምሳጋ ካለሁለት ታንኮች በስተቀር ኣላቃጠልንም። እነሱም ምሽግ ካልሰበርን ብሎ በጣም ስለረበሹንና ኣማራጭ ስላጣን እንጂ እንድንይዛቸው ነበር ፍላጎታችን። ደርግ የማቃጠሉን ስራ ጀመረ። ምናልባት ካልረሳሁት ኣንድ ኣውቶቡስ ኣንድ ታንክ ኣንድ የጭነት መኪናና ሁለት ወይም ሶስት ኦራሎች ሲቃጠሉ፡ ሶስት ቢኤም40ና ከ100 በላይ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ማስቀረት ችለናል። ይህ ንብረት የኢህኣዴግ ንብረት እንዲሆን ያደረጉ ሁለት ወይም ሶስት ታጋዮች ነበሩ። ይህንን ስራ ለመስራት ሲታቀድ ህወሓት/ኢህኣዴግ ምን ማድረግ እንዳለበትና እንደሚይችል ኣውቀ ነበር። በዛን ስራ ዓቅሙን ኣውቆ ነበር ስራውን የጀመረው።

በፅሑፌን መጀመርያ ኣመድበር መድረስችን ገሊጬ ነበር ወደ ደብረታቦር ጦርነት የወሰድኳቹህ። እንግዲህ እኔ ጋ እየተጓዛቹህ ከሆነ ኣመድበርን ኣልፈን ተጉዘን ኣንድ ስዓት ባልበለጠ ርቀት በራሃ ላይ እንድንውል ተደረገ። ከስዓት 9፡00 ስዓት መሆኑ ነው ተነስተን ተጉዘን ወረታ ከተማን ከሩቅ ማየት በምንችልበት ቦታ እንደደረስን ወረታን እንደምናጠቃ ተነግሮን ብዙ ሳንዋጋ ወረታን ተቆጣጠርናት። ስራው ከተጠናቀቀ ከተወሰኑ ሰዓታት በኋላ ጉዞ ወደ ሰሜን ኣዲስ ዘመንንንም ተቆጣጠርናት። ለቀናት እንደቆየን ያልተጠበቀ ነገር ተፈጠረ። ደርግ ጎንደርና ባሕርዳርን በፈቃዱ ሳናስገድደው መልቀቅ ጀመረ። ይህ ሁኔታ እንደተፈጠረ (ታጋዮች) ጎንደርንና ባሕርዳር ከተሞች ያለምንም ጦርነት በቁጥጥራችን ስር እንደሚሆኑ ወሬውን ሲደርሰ ተደሰትን። ከስዓት በኋላ ዝግጅታችን እንደጨረስን ጉዞ ወደ ምስራቅ ወደ ደብረታቦር ኣቅጣጫ ጀመርን ግራ ተጋባን። ከኣንድ ስዓት መንገድ በኋላ ለተወሰነ ግዜ ዕረፍት ተሰጥቶን ስብሰባ ተደረገ።

የሬጅመንት የፖለቲካ ሓላፊያችን “የት የምንሔድ ይመስላቹሃል”? ብሎ በጥያቄ ንግግሩን ጀመረ። የሁላችንን መልስ በኣንድ ላይ “ደብረታቦር” ብለን ስንመልስ እሱም ንግግሩን በመቀጠል“ትክክል ናቹህ። ምናልባት ያልሰማቹ ካላቹ ደርግ ባሕርዳርና ጎንደርን ከተሞች ለቆ መሔድ ጀምረዋል። ከከተሞቹ ደርግ ለቆ መሔዱን ካለ መስዋእትና ልፋት ብንይዛቸው ባልከፋ ነበር። ሆኖም ግን ከጥቅሙ ጉዳቱን ስለሚበልጥ ወረታና ኣዲስ ዘመን በመልቀቅ ደርግ ባለበት እንዲይቆይ ስለሚረዳው ድርጅታችን ሓይላችን ባጠቃላይ በደብረታቦር ኣካባቢ ብቻ እንድንቆይ ተወስነዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት ሁለቱም ትላልቅ ከተሞችን ለማስተዳደር ኢህኣዴግ ኣቅሙን ስለማይፈቅድለትና ስላልተዘጋጀበት በከተሞቹና በህዝቡ ጉዳት እንዳይደርስ ከማለት ደርግ ከተሞቹን እያስተዳደረ እንዲቆይ ተፈቅዶለታል።” ብሎ ቁምነገሩን ካስተላለፈ በኋላ “ኣትርሱ ማንኛውም ነገር እኛ ስንፈቅድ እንጂ ደርግ

በገዛ ፈቃዱ ማንኛውም ነገር መስራትም ኣይገባውም። ስለዚህም ነው ድርጅታችን ደርግ ባደረገው ነገር ተበሳጭቶ ደርግ ያሰበውን እንዳይፈፅም እንድንመለስ ያዘዘን" ብሎ ቀልዱም ያከለበት።

እላይ ከገለፅኩት 20 ዓመታት ያስቆጠርውን ታሪክ ምን ማለት ይቻላል ስለኢህኣዴግ? በዛን ወቅት በጦርነቱም ሆነ በኣስተዳደር ስራ ከመስራቱ በፊት የግዜው ሁኔታዎች በመገምገም ሁኔታዎቹን ለመጠቀምና ላለመጠቀም ውሳኔ ላይ ለመድረስ በመጀመርያ ዓቅሙን ይመረምራል ኢህአዴግ። ማድረግ ለማይችለው ነገር ለመፈፀም ኣይሰማራም። ኢህኣዴግ ለማንኛውም ነገር ሲመረምር በመጀመርያ መመዘኛው ይህንን ነገር ቢይደረግ ወይም ባይደርግ ለህዝብ ምን ይጠቅማል? ምንስ ይጎዳል? የሚይለውን ጥያቄ መልሶ ነው ወደ አንድ ውሳኔ የሚይደርሰው። ለምን ብትሉኝ ህወሓት/ኢህኣዴግ ከህዝብ ለህዝብ የተፈጠረ ድርጅት ከመሆኑ የተነሳ ስለሆነ ነው።

ህወሓት/ኢህኣዴግ ዓቅሙን የሚይመዝንና ዓቅሙን የሚይፈቅድለት ብቻ ለመስራት የሚይሰማራ ድርጅት ለመሆኑ ስእሉን ማስየት የሚያስችሉ የ34 ዓመታት ብዙ ታሪኮች ኣውርተህ የማያልቁ ኣሉት። ህወሓት/ኢህኣዴግ የትጥቅ ትግሉን በኣሸናፊነት እንዲወጣና ኣሁንም ሰላማዊ ትግሉን ብድል እየተወጣው ያለበት ምክንያት ሚስጥሩን ህዝባዊ ዓላማውና ወገንነቱን፡ ዓቅሙን የሚያውቅበትና በዓቅሙ ልክ መሔድ የሚይችልበት ባህሪ ስላለው ብቻ ነው። ሌላ ምንም ዓይነት ሚስጥር የለውም።

ስለሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችስ ምን ማየት እንችላለን? ስለድርጅቶቹ ታሪክ ተናግሮት ኣልፈዋል። ታሪክ ዓቅማቸውን ማወቅ እንደማይችሉና ዓቅማቸውን ለማየት ባህሪም እንደሌላቸውም ታሪክ መስክሮታል። ቢሆንም ታሪክ ለማያውቀው ማሳወቅ ለረሳው ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል። ሃጼ ሃ/ስላሰ ንግስነታቸውን ኣጥቶ ደርግ ስልጣን በያዘበት ግዜ ነበር ብዙ ድርጅቶችን በከተሞችና በበረሃ እንቅስቃሴ የጀመሩት። ከድርጅቶቹ ኣንዱ ኢህኣፓ ነበረ።

በዛን ግዜ በሰው ሓይልና በምሁራንና ተማሪዎች ብዛት ትልቁን ቁጥር የያዘው ኢህኣፓ ነበረ።

1) ትግል ከከተማ ወደ ገጠር የሚይለውን ስልት በመያዝ ነበር ሲታገል የነበረው። ኣንድ እስከ ኣፍንጫው የታጠቀ መንግስት ይህ የሚባል መሳርያ ባልታጠቀው ራሱን ለመከላከል በማያስችለው ኣደረጃጀት ሆኖ ደርግን ኣስሸንፋሎህ በማለት ስራውን ተያያዘው።
2) ይዞት በተነሳ ጥያቄም ብሔራዊ ጥያቄ ይዞ መታገል ጠበብተኝነት ነው በማለት የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታን በሚገባ ባለመገንዘቡን ከዓቅሙ በላይ መሸከም የማይችለውን ጥያቄ በመሸከም ለመረማመድ ሞኩረዋል።
3) ኢህኣሰም ቢሆን (የኢህኣፓ የታጠቀ የበረሃ ሓይል) በህወሓት ኣብሮ የመስራትና ልዩነቶችን ለማጠብብ ለተደረገለትን ጥሪ ሳይቀበል ቀርቶ ሳያበቃ ህወሓት ለማጥፋት በህወሓት ላይ ጦርነት ኣውጆ በጀመረው ጦርነት ራሱን ተቀበረበት።

4) በ1983 ኢ.ህኣፓ እንደ ሌሎች የኢትዮጲያ ድርጅቶች በህወሓት/ኢ.ህኣዴግ በሽግግር መንግስቱን ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ ቀርቦለት ጥሪውን ከመቀበል ይልቅ በህወሓት ላይ ጦርነት አወጀ።

በሱዳን ለሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ስብሰባ ተደርጎላቸው በኢ.ህኣፓዎች እንደ ማይቀበሉት ገልፆ በህወሓት/ኢ.ህኣዴግ ላይ ጦርነት እንዳወጁ ስብሰባው ውስጥ ስይናገሩ በዛን ግዜ ኣምባሳደር ኣዲስኣለም ባሌማ “ጦርነት ለሁሉም ኣይበጅም። በተለይ በተለይ ለኢ.ህኣፓ ኣይበጅም።” ብሎ ምክሩን ለግሶላቸው ነበር። በኣራቱቱም መመዘኛዎች ኢ.ህኣፓን ስንቃኘው ኢ.ህኣፓ ዓቅሙን ኣውቆ የተደራጀና የሰራ ድርጅት ኣልነበረም። ስለዚህም ይመስለኛል ህወሓት በትጥቅ ትግሉ ዘመን “ወጣ ወጣ ኣለና እንደ ሻምበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቆጮ” ብሎ ስለኢ.ህኣፓ የፃፈው። ኢ.ህኣፓ ታሪክ ሆኖ እንዲቀርና እንዲ ነገርለት ምክንያት የሆነው ራሱ ኢ.ህኣፓ እንጂ ሌላ ሓይል ኣይመስለኝም።

ኢ.ህኣፓ ተሸንፈዋል። ለሽንፈቱ ህወሓት ኣስተዋፆ ኣለው። በጦርነት ዓለም ተፋልመዋልና። ለሽንፈቱን ወሳኙ ሚና የተጫወተው ግን ራሱ ኢ.ህኣፓ ነው። ዓላማው ባህሪው ስልቱን ሁሉም ስህተት ስለነበሩ ለሽንፈቱን ምክንያት ነበሩ።ቅንጅትም እንደሌሎቹ ታሪክ ሆነዋል። የቅንጅት መስራቾች የኢ.ህኣፓ ሰዎች ናቸው። በኢ.ህኣፓ የሰሩት ስሕተቶች ታሪክ እንደገና ደግሞታል። ታሪክ ራሱን የደገመበት ምክንያት ለማወቅ የተወሳሰበ ምርምር ኣያስፈልገውም። ምክንይቱም

1) ህዝባዊ ወገንነት ኣልነበረውም። የምርጫው ሓቀኛ ውጤት ለመቀበል ዓቅም ኣልነበራቸውምና።
2) ኢ.ህኣዴግን በንግግር ሳይሆን በስራ ምንያህል እንደ በለጣቸው ለኢ.ትዮጵያና ህዝብዋ ምን ያህል ታማኝነት እንዳለበት ለማየት ዓቅሙን ኣልሰጣቸውምና።
3) ድርጅት እንዴት እንደሚመሰረትና እንዴት መስራት እንደሚገባው ለማወቅ ዓቅሙን ኣልተፈጠረላቸውምና።

ዓቅምህን ማወቅ ካልተቻለ ሂወትን መምራት በጣም ትልቅ ፈተና ነው። እንኳን ሃገርንና ህዝብን ለመምራት። ይህንን ዓቅምን የማወቅ ዕድል ብዙ ድርጅቶች ሊያገኙት የሚይችል ኣጋጣሚ ኣይኖርም። በእኔ ኣስተሳሰብ ወገንነትን ይጠይቃል ብየ በፅኑዕ ኣምናለሁኝ። የህዝብ ወገነት ከስማይ የሚይዘንብ ነገር ኣይደለም። ከባህሪህ የሚመጣ ጉዳይ ነው። ከዚህ በመነሳት በኣሁኑ ግዜ የዚህን ዕድል ተጠቃሚ የሆነው ኢ.ህኣዴግ ብቻ ነው።
ኣንድ ኣንድ ድርጅቶች ዓላማቸውን በሚገባ ያወቁ ኣይመስለኝም። ይህንን ለማለት ያስቻለኝ እኔ ባለሁበት ሃገር ኣንድ ግዜ ባለፈው የኢ.ትዮጵያ የምርጫ ግዜ ድርጅት እንመስርት የሚይሉ ሰዎች ስብሰባ ጠሩን። እኛም ኣላሳፈርናቸውም። በቦታው ተገኘኝ። ኢ.ህኣዴግ መውረድ ኣለበት። ይህንን ስራ ለመስራትና ለመደራጀት ነው ስብሰባው የጠራነው ኣሉን። ብዙ ያሉትን ነገር ነበረ። ያንን መተንተኑን ግዜ ማጥፋት ይሆንብኛል። ምክንያቱ እናንተም ከሌሎዎቹን የምትሰሙት ተመሳሳይ ነገር ነውና። በተሰብሳቢዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ነበሩ። ከጥያቄዎቹ

- ኢ.ህኣዴግ መውረድ ካለበት ኢ.ህ ኣዴግን መተካት ይቻላል ወይ? በማን?
- ኢ.ህኣዴግን የሚተካው ድርጅት ምን ያህል ኣስተማማኝና ምን ያህል የዘጋጀ ድርጅት ነው?
- የድርጅቱ ስምና ዓላማስ ምንድነው?
- ኢ.ህ ኣዴግ በሰላም ማውረድ ሳይቻል ሲቀርስ የትጥቅ ትግል ያስፈጋል ወይ? ካስፈለገስ በኣሁኑ ግዜ በኢ.ትዮጵያ የትጥቅ ትግል ለማካሔድ ህዝቡ ይፈልገዋል ወይ? ምን ያህልስ ህዝብን ማሳተፍ ይችላል? የሚሉ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች ኣስቅኝ ነበሩ።

ከተሰበሰብነው ሰዎች ኣንድም ትክክል ናቹህ ብሎ የደገፋቸው ኣልነበረም። ጥቂቶችን ማሳመን ያልቻሉ ፖለቲከኞቻችን ኢ.ትዮጵያን ማስተዳደር ምን ያህል ይከዳቸው ይሆን? እኔ በጣም ነው ያዘንኩላቸው። የግድም ማዘን ይኖርብኛል ለነሱ ስል ነበር በርሃ ላይ ስንከራተት የነበርኩትና። ዓቅማቸውን በሚገባ ለማወቅ ምን ያህል ችግር እንዳላቸው ብያውቁት እንዴት ጥሩ ነበረ?

የፖለቲከኞቻችን ጨዋታ ተወርቶ ኣያልቅም። ለዛሬ በዚህ ልለያቹህ።

ሃይለ/ተጋዳላይ 08/02/09